የሰ/መ/ቁ. 35621

ጥቅምት 11 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ሰንሻይን ኮንስትራክሽን - አልቀረበም

**መልስ ሰጭ፡-** 1. አቶ ፍቃዱ ገቢሣ - አልቀረቡም

2. አቶ ታዬ ዋሚ - ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የታች ተከሣሽ ሲሆን የአሁን መ/ሰጭ የታች ከሣሾች ነበሩ፡፡ መ/ሰጭ በታች ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት በመቀጠር በአናፂነት ሙያ ሲያገለግሉ ቆይተው ሌላ ሣይት (ቦታ) ሥራ እያለው ሥራው አልቋል በማለት ያለ ቅድመ ማስጠንቀቂያ የሥራ ውላችንን አቋርጦብናል ስለዚህ የአገልግሎት ክፍያ የማስጠንቀቂያ የሁለት ወር የዘገየበት የስንብት የስድስት (6) ወር ክፍያ እና የትርፍ ሰዓት ክፍያ እንዲወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡

ተከሣሽ (የአሁን አመልካች) ጥቅምት 27 ቀን 1999 ዓ.ም በጽሁፍ ባቀረበው መልስ ከሣሽ (መልስ ሰጭ) ደመወዝ የሚከፈላቸው በቀን ታስቦ እንደሆነና ከአመልካች ድርጅት ጋር የፈፀሙት ጊዜያዊነት ያለው የሥራ ውል የተመደቡበት የአናፂነት ሥራ በሚኖርበት ጊዜ ብቻ የሚከፈላቸው መሆኑን ገልጾ የስራ ውሉ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 24(1) መሰረት በሕጋዊ መንገድ እንደተቋረጠ በመግለጽ ተከራክሮ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የመልስ ሰጭ የሥራ ውል መቋረጡ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ጭብጥ ይዞ መዝገቡን መርምሮታል፡፡ በዚህም መሰረት በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10(1) (ሠ) መሰረት ሥራው ምንም እንኳ የአሠሪው ቋሚ ሥራ ቢሆንም አልፎ አልፎ የአናፂነት ሥራው ሲኖር የሚሰራ መሆኑን ተረድቻለሁ በማለት አመልካች መልስ ሰጭን ማሰናበቱ በአዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 10(1)(ሀ) መሰረት በአግባቡ ነው ሲል ወስኗል፡፡

መልስ ሰጭም በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት የታች ፍ/ቤት ማስረጃ ሣያጣራ ወሰነብን በማለት ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቤቱታቸውን አቅርቧል፡፡

የከፍተኛው ፍ/ቤትም በቀረበለት አቤቱታ መሰረት የአሁን አመልካች መልስ እንዲሰጥበት ካደረገ በኋላ ይግባኝ ባይ (የአሁን መልስ ሰጭ) የተቀጠሩት ለየትኛው ፕሮጀክት ነው? ፕሮጀክት በመጠናቀቁ ነው ወይስ አይደለም የተሰናበቱት? የሚለውን ጭብጥ መሥርቶ ከመረመረ በኋላ በቅጥር ውል ላይ “ለምን ስራ፣ እስከመቼ” የሚለውን የሚያስረዳ ባለመሆኑ የአሁን መልስ ሰጭ (የታች ከሳሽ) የተቀጠሩት በአዋጁ አንቀጽ (10) ስር በተደነገጉት መሰረት ነው ተብሎ የሚወሰድበት ምክንያት የለም በማለት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በመሻር ስንብቱ ያለ አግባብ ነው በማለት ለአሁን መልስ ሰጭ የ8 ወር ውዝፍ ደሞዝ እንዲከፈላቸውና ወደ ምድብ ስራቸው እንዲመለሱ ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታም የቀረበው የከፍተኛው ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻሩ ቅር ተሰኝቶ ሲሆን የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የጉዳዩን አመጣጥ ካጠና በኋላ የሥር ፍ/ቤት ማስረጃ መስማት እየቻለ መልስ ሰጭ የተቀጠረበት ሥራ መጠናቀቁ እየተገለፀ ወደ ሥራ ይመለሱ መባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩን አስቀርቦታል፡፡ በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱትን ጭብጦች በመያዝ ግራ ቀኙ በጉዳዩ መልስ እና የመልስ መልስ እንዲያቀርቡ በማድረግ አከራክሯል፡፡

በታች የተሰጡትን ውሳኔዎች ከህጉ በማገናዘብ እንዳየነው መልስ ሰጭ "በፊንጫ ለምለም" ፕሮጀክት ውስጥ በአናፂነት ሥራ ሲሰሩ እንደቆዩ በመግለጽ ሥራ በሌላ ሣይት (ቦታ) እያለ ሥራ አልቋል በመባል መሰናበታቸው ከሕግ ውጭ ነው ሲሉ ባቀረቡት ክስ መሰረት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን አከራክሮ ስንብቱ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10(1) (ሀ) መሰረት ሕጋዊ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለትም የከፍተኛው ፍ/ቤት የመልስ ሰጭ የቅጥር ሁኔታ በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 10(1)(ሠ) ከተዘረዘሩት ውጭ ስለሆነ ስንብቱ ህጋዊ አይደለም በማለት የተጠየቀውን ክፍያ እንዲከፍላቸውና ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ በመወሰን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሰረት የታች ውሳኔን ሽሮታል፡፡

በመሰረቱ ከላይ ከተነሱት ክርክሮች መገንዘብ እንደተቻለው መልስ ሰጭ በአመልካች ድርጅት ለምን ስራ እንደተቀጠሩ በሚለው ነጥብ ቀድሞውንም አልተከራከሩም (አልተካካዱም) የአናፂነት ሥራ ደግሞ በግንባታ ሥራ ውስጥ ወቅቱን ጠብቆ የሚሰራ እና ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የተጀመረው ግንባታ እንደሚጠናቀቅ ግልጽ ሆኖ ሳለ ለምን ስራ እና እስከመቼ ይሰራሉ? የሚለውን ነጥብ ማየቱ በተያዘው ጉዳይ አግባብነት የለውም፡፡ መልስ ሰጭ ቢሆኑም በክሳቸው ውስጥ ድርጅቱ ሌላ ቦታ(ሣይት) እንዳለው በመግለጽ ሥራው አላለቀም በማለት ይከራከራሉ፡፡

በመሰረቱ በሌላ ቦታ ተጨማሪ (ተመሣሣይ) ሥራ መኖሩ የተባለውን የፕሮጀክት ሥራ አላለቀም የሚያስብል አይሆንም፡፡ ድርጅቱም የግድ ከአንድ ፕሮጀክት ወደ ሌላው ፕሮጀክት ሰራተኞችን ይዞ እንዲዞር የሚያስገድደው የሕግ ነጥብ አይኖርም፤ ምክንያቱም ድርጅቱ የራሱ የሆነ የአሰራር ስርአት ይኖረዋል ተብሎ ስለሚገመት፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የሥራውን መጠናቀቅና መኖር በድጋሚ በማስረጃ ማጣራት እየተቻለ ይህ ሣይደረግ በከፍተኛው ፍ/ቤት ስንብቱ ያለ አግባብ ነው መባሉና መልስ ሰጭ የጠየቁት ክፍያ ተከፍሎአቸው ወደ ስራቸው ይመለሱ ተብሎ መወሰኑ የአዋጁን አንቀጽ 10(1) (ሠ)"ን" ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23063 በሰኔ 6 ቀን 1999 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ ፀንቷል ይፃፍ፡፡
2. በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57553 በታህሳስ 22 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ ስንብቱ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ